የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፻፭
አዲስ አበባ ነሐሴ ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

33th Year No.105
Addis Ababa 15th, August 2025


**ማውጫ**


**ደንብ ቁጥር ፻፺፭/፪ሺ፲፯**

**የመሬት ይዞታ መብት ፈጠራ እና አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር ፻፷፫/፪ሺ፲፮ን ለማሻሻል የወጣ ደንብ**

**ገጽ ........................................... ፬ሺ፲፩**


**CONTENT**


**REGULATION NUMBER 195/2025**
**A REGULATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF LAND HOLDING RIGHTS CREATION AND SERVICE DELIVERY REGULATION NUMBER 163/2024**

**Page ........................................... 4011**


## ደንብ ቁጥር ፻፺፭/፪ሺ፲፯
## የመሬት ይዞታ መብት ፈጠራ እና አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር ፻፷፫/፪ሺ፲፮ን ለማሻሻል የወጣ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ አስተዳደር አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድላቸው ቦታዎችን የያዙ ነዋሪዎች መብት ተፈጥሮላቸው የይዞታ መብት ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የተከናወኑ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ጊዜ የወሰዱ በመሆናቸውና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ የሚያስችል ነባራዊ ሁኔታ ባለመኖሩ እና አገልግሎቱን ሰጥቶ ለማጠናቀቅ ተጨማሪ ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፭ አንቀጽ ፺፬ መሰረት ይህን ማሻሻያ ደንብ አውጥቷል፡፡

## REGULATION NUMBER 195/2025
## A REGULATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF LAND HOLDING RIGHTS CREATION AND SERVICE DELIVERY REGULATION NUMBER 163/2024

**WHEREAS,** the preparation activities being undertaken to ensure the rights of residents of the city that hold land without the permission of the relevant organ of the Addis Ababa city government land holding administration have taken longer time and as there is no existing practical situation to finalize the thereof and the activities demand additional time;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 94 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Specify the Powers and Duties of the thereof Proclamation Number 84/2023, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this Regulation.


ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የመሬት ይዞታ መብት ፈጠራ እና አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር ፻፷፫/፪ሺ፲፮ን ለማሻሻል የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፺፭/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"አዋጅ"** ማለት የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፯፻፳፩/፪ሺ፬ ነው፤

፪. **"ደንብ"** ማለት የመሬት ይዞታ መብት ፈጠራ እና አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር ፻፷፫/፪ሺ፲፮ ነው፤

፫. በደንቡ የተተረጎሙ ቃላትና ሐረጎች በዚህ ደንብም ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

**፫. <u>ማሻሻያ</u>**

የመሬት ይዞታ መብት ፈጠራ እና አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር ፻፷፫/፪ሺ፲፮ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩. በደንቡ አንቀጽ ፶፪ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፤

"፩. እስከ ሚያዚያ ፴ ቀን ፩ሺ፱፻፺፯ ዓ.ም ድረስ አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድላቸው የተያዙ መብት ያልተፈጠረላቸው ይዞታዎች አዋጁ ከወጣ በኋላ በከተማ አስተዳደሩ ጥሪ ተደርጎላቸው ለቢሮው ቦታውን ስለመያዛቸው የሚያስረዳ ሰነድ አቅርበው ካርታ እንዲሰራላቸው ለሚጠብቁ ባለይዞታዎች ይህ ደንብ ጸድቆ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመት ብቻ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፤"

**፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከነሐሴ ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ ደሳ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**1. <u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as: "Land Holding Rights Creation and Service Delivery Regulation Number 163/2024 Amendment Regulation Number 195/2025."

**2. <u>Definition</u>**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"Proclamation"** means Urban Lands Lease Holding Proclamation Number 721/2011;
2. **"Regulation"** means the Land Holding Rights Creation and Service Delivery Regulation Number 163/2024;
3. The definitions given in the Regulation are effective in this Regulation.

**3. <u>Amendment</u>**

The Land Holding Rights Creation and Service Delivery Regulation Number 163/2024 is amended as follows:

1. Sub-Article (1) of Article 52 of the Regulation is revoked and replaced by the following new Sub-Article (1):

"1. Land holders, who have submitted documents and waiting for the issuance of a title deed upon the request of the city administration after the issuance of the Proclamation for occupying a land until May 8, 2005 without the permission of the relevant organ and did not possess rights, shall obtain the service from the bureau for only two years starting from the effective date of the Regulation."

**4. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force as of this 15th day of August 2025.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of August 2025.**

**AdanechAbiebieDessa**
**Mayor of Addis Ababa City**